የዱር እንስሳት ጥናት፤ልማት ጥበቃና አጠቃቀም ዋና የስራ ሂደት በአዊ ብሄረሰብ አስተዳደር ዞን



በዘንገና በጢርባ ዘንገና ሐይቅ፣ በወርኪ እና በዱቲ ዉሃ አዘል መሬቶች፤*በፏንግ፤በዶንዶርና በጋርቾ ፏፏቴዎችና በዳንጉላ ዋሻዎች የሚገኙ የዱር እንስሳት፤አጽዋትና ተፈጥሯዊ ገፅታ ጥናት*

አበጀ ዘዉዴ

በልስቲ ፈጠነ

መስከረም 2004 ዓ.ም

ማውጫ

1. መግቢያ 1
2. ዓላማ 3
3. ጥናቱ የተከናወነባቸው ቦታዎች 3
3.1. የዘንገና ሐይቅ፣ የወርኪ እና የዱቲ እርጥብ አዘል መሬቶች አካባቢ፣ 3
3.2. የፋንግ ፉፉቴ፣ 4
3.3. የጥርባ ሐይቅ፣ 4
3.4. የዳንጉላ ዋሻዎች፣ 4
3.5. የደንደር ፏፏቴ፣ የጋርቾ ፏፏቴ እና የቻግኒ ከተማ አካባቢ፣ 6
3.6. የጓንጓ ኢላላ ጥብቅ የመንግስት ደን፡ 6
3.7. ትሰኪ ፏፏቴ 7
4. በጥናቱ ጥቅም ላይ የዋሉ ስልቶችና ቁሳቁሶች 7
4.1. በጥናቱ ጥቅም ላይ የዋሉት ስልቶች 7
4.2. በጥናቱ ጥቅም ላይ የዋሉ ቁሳቁሶች 7
5. በመስክ የተከናወኑ ተግባራት 7
6. ከጥናቱ የተገኙ ውጤቶች 8
7. በመምሪያው ወደ ፊት መከናወን ያለባቸው ተግባራት 9
8. ያጋጠሙ ችግሮች 9
9. አባሪ 10
9.1. List of Plants Registered in and around Tourist attraction sites in Awi Zone 10
9.2. List of Birds Registered in and around Tourist attraction sites in Awi Zone 14
9.3. List of Mammals Observed by Locals and study team 15
9.4 Photographi representation of Birds seen in Awi Zone 16

1. መግቢያ

የአዊ ብሔረሰብ አስተዳደር ዞን በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ውስጥ የሚገኝ ሲሆን በውስጡ 7 የገጠር ወረዳዎች፣ 3 የከተማ አስተዳደሮች እና 188 ቀበሌዎች (21 የከተማ እና 167 የገጠር) ይገኛሉ። የአየር ንብረቱ ከደጋ እስከ ቆላ ያለውን ያካትታል። ዞኑ ከዚህ ቀደም በተካሄዱ ጥናቶች የተለያዩ የዱር እንስሳት፣ ዕፅዋት እና አእዋፋት መኖሪያ እንደሆነ ተጠቁሟል።

በመሆኑም በውስጡ የሚገኙ ዋና ዋና መስህብ ቦታዎች በአግባቡ ለምተውና ተጠብቀው ወደ ቱሪዝም ገቢያ እንዲገቡና የአካባቢው ህብረተሰብ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ የዞኑ ባህልና ቱሪዝም መምሪያ ባቀረበው ጥያቄ መሰረት ቢሮው ሁለት ባለሙያዎችን በመላክ በዞኑ ውስጥ በዋና ዋና መስህብ ሃብቶች አካባቢ የሚገኙ ዕፅዋትና እንስሳት እንዲለዩና እንዲጠኑ ተደርጓል።

ስለሆነም የዘንገና ሐይቅ፣ የወርኪና ዱቲ እርጥብ አዘል መሬቶች አካባቢ፣ የፋንግ ፏፏቴ፣ የዳንጉላ ዋሻና ጥርባ ሐይቅ፣ የዶንደር ፏፏቴ፣ የጋርኞ ፏፏቴና እና የጓንጓ ኢላላ የመንግስት ጥብቅ ደን እንዲሁም የትስኪ ፏፏቴ የተፈጥሮ መስህቦች ዝርዝር የብዝሃ ህይወት ሃብት ጥናት ተካሂዶ ውጤቱም እንደሚከተለው ቀርቧል።

2. ዓላማ

በአዊ ብሄረሰብ አስተዳደር ዞን ውስጥ በሚገኙ በዶንደር፣ ጋርኞ፣ ትስኪና ፋንግ ፏፏቴዎችና በዘንገናና በጥርባ ሐይቆች፣ በወርኪና ዱቲ እርጥብ አዘል መሬቶች አካባቢ የሚገኙ አገር በቀል የሆኑ የእፅዋትና የእንስሳት ዝርያዎችን ለመለየትና ሌሎች መስህብነት ያላቸው የተፈጥሮ ገጽታዎች ጉልተው ወጥተው ወደ ቱሪዝም ገበያ እንዲገቡ ማድረግ፣

3. ጥናቱ የተከናወነባቸው ቦታዎች

በአዊ ብሄረሰብ አስተዳደር ዞን በተለያዩ ወረዳዎች ውስጥ በሚገኙ ዋና ዋና የመስህብ ቦታዎች፡-

3.1. የዘንገና ሐይቅ፣ የወርኪ እና የዱቲ እርጥብ አዘል መሬቶች አካባቢ፣

ይህ ሐይቅ በባንጃ ሽኩዳድ ወረዳ በከሳ ቾውሳ ቀበሌ ውስጥ ከእንጅባራ ከተማ 5 ኪ.ሜ ርቀት እንዲሁም ከአዲስ አበባ ባህር ዳር መስመር 100 ሜትር ርቀት በ$10^0$54’47” ሰሜን ላቲቲዩድና በ$36^0$57’45” ምስራቅ ሎንግቲውድ ከባህር ወለል በላይ በ2523 ሜትር ከፍታ ላይ ይገኛል። አፈጣጠሩ በእሳተ ጎመራ ሲሆን ወደ 50 ሄ/ር የሚጠጋ ስፋት እንዳለው ይገመታል። ወደ ጎን በአማካኝ ከ800 ሜትር በላይ ርዝመት ያለው ሲሆን ጥልቀቱ ከ150 ሜትር በላይ እንደሆነ ይታመናል። የሐይቁ ዙሪያ በአብዛኛው በሰው ሰራሽ ደን ማለትም ባህር ዛፍ፣ የፈረንጅ ዕድ፣ ፓይነስ ፓቹላ የተያዘ ሲሆን አልፎ አልፎ በተፈጥሮ ዕፅዋት ማለትም ሾላ፣ ዋርካ፣ የሃበሻ ግራር፣ ጨባ የተሞላ ነው (ዝርዝሩን በአባሪ 9.1 ላይ ይመልከቱ)። ከአጥቢ የዱር እንስሳት መካከልም ጉሬዛ እና ሽኮኮን ለማየት የሚያስችል ቦታ ነው። ከዚህ በተጨማሪም በሐይቁ አካባቢ በቅርብ ርቀት ላይ በሚገኙት የወርኪና ዱቲ እርጥ አዘል መሬቶች ውስጥ ከዋና ዋና አእዋፍት መካከል ፔሊካንስ፣ ሄሮንስ፣ ኪንግ ፊሸርስ፣ የተለያዩ የዳክዬ ዝርያዎች፣ ሁለት ዓይነት የጀቢራ ወይም ጥንብ አንሳ ዘርዎች፣ የ3 ዓይነት

የስቶርክ ዝርያዎች፣ 3 ዓይነት የጋጋኖ ዝርያዎች፣ 3 ዓይነት የቁራ ዝርያዎች፣ ሁለት ዓይነት የኢግሬት ዝርያዎች እንደሚገኙ ታውቋል። ከዚህ በተጨማሪ በእንጅባራ ከተማ በሚካኤል ቤተክርስቲያን ውስጥ በኤርትርና እና በሀገራችን ብቻ የሚገኙትን ብርቅየ አእዋፋት ባለ እንጥልጥል ጋጋኖ እና ቲክቢልድ ራቨን ጨምሮ በርካታ የአእዋፍት ዝርያዎችን በጠዋትና በማታ ስዓት መመልከት ለሚሹ ሁሉ ምቹ ቦታ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል።

3.2. የፉንማ ፋፋቴ፣


ይህ ፏፏቴ በጓጉሳ ሽኩዳድ ወረዳ በወንጀላ አጉታ ጓስታ እና በአስኩና አግዛ እግዚአብሄር አብ ቀበሌዎች መካከል ውስጥ ከትሊሊ ከተማ 2.3 ኪ.ሜ ርቀት $10^0$49’44” ሰሜን ላቲቲዩድና በ$37^0$00’50” ምስራቅ ሎንግቲውድ ከባህር ወለል በላይ በ2401 ሜትር ከፍታ ላይ ይገኛል። ፏፏቴው በፈጣም ወንዝ በ40 ሜትር ገደል ላይ የተፈጠረ ሲሆን በኤርትርና እና በሀገራችን ብቻ የሚገኙትን ብርቅየ አእዋፋት ባለ እንጥልጥል ጋጋኖ፣ አንገተ ነጭ እርግብ እና ራሰ ጥቁር ጨጭ በተለይም የባለ እንጥልጥል ጋጋኖ የወፍ ዝርያ ዋነኛ መራቢያና መኖሪያ እንደሆነ ታውቋል። በተጨማሪም ፏፏቴው ዙሪያውን ወንዙን ተከትሎ እስከ ወንጀላ ገብርኤል ንዑስ ቀበሌ ድረስ በደን የተሸፈነ ሲሆን በውስጡ ከሚገኙት ዕፅዋት መካከልም የሐበሻ ግራር፣ ጨባ፣ ሾላ፣ ቀርቅሃ፣ ሰሳ፣ ውልክፋ፣ ኮርች፣ ኮሶ፣ ኮማ፣ ገተም ዋና ዋናዎቹ ናቸው (ዝርዝሩን በአባሪ 9.1 ላይ ይመልከቱ)። ከአጥቢ የዱር እንስሳት መካከልም ጉሬዛና ጦጣ እንደልብ የሚታዩ ናቸው።

3.3. የጥርባ ሐይቅ፣

ጥርባ ሐይቅ በአንክሻ ጓጉሣ ወረዳ ውስጥ የሚገኝ ሐይቅ ነው። ከአገው ግ/ቤት ማርያም ከተማ 6 ኪ.ሜ ያህል የሚርቀው ይህ ሐይቅ በ3ቱ ጥርባ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ በ$10^0$49’59” ሰሜን ላቲቲዩድና በ$36^0$50’56” ምስራቅ ሎንግቲውድ ከባህር ወለል በላይ 2221 ሜትር ከፍታ ላይ ይገኛል። አፈጣጠሩ ልክ እንደ ዘንገና ሐይቅ በእሳተ ጎመራ የሆነው ይህ ሐይቅ ወደ 60 ሄ/ር የሚጠጋ ስፋት እንዳለው ይገመታል። ወደ ጎን በአማካኝ ከ900 ሜትር በላይ ርዝመት ያለው ሲሆን ጥልቀቱ ከ155 ሜትር በላይ እንደሆነ ይታመናል። ከመሬት ወደ ሐይቁ ተዳፋቱ የሚጨምረው ይህ ክሬተር ሐይቅ ዙሪው በዕፅዋት የተሸፈነና ውስጡ በውሃና ከእሳተ ጎመራው ፍሳሽ በጠጠሩ ቀላልና በከፊል የተቃጠሉ ድንጋዮች የተያዘ ነው። በሐይቁ ዙሪያ ያለው የዕፅዋት ሽፋን ወደ ሐይቁ ደለል እንዳይገባ ሲከላከል በሐይቁ ዙሪያ ካለው ዕፅዋት ውጭ ያለው መሬት ተዳፋቱ ወደ አጎራባች መሬቶች በመሆኑ የጎርፍ ችግር የሚያስጋው አይደልም።

በሐይቁ አካባቢ በቅለው ከሚታዩ ዕፅዋት መካከል ሾላ፣ ዝግባ፣ ድንጋይ ሰበር፣ ብሳና፣ ዋንዛ፣ ዋርካ፣ ኮማ፣ ገተም ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ብሳና እና ሾላ በብዛት የሚታዩ የዕፅዋት ዓይነቶች ናቸው። ከዚህ ሌላ የዱር አሳማ፣ ከርከሮ፣ ድኩላ፣ ተራ ዝንጀሮ፣ ጉሬዛ፣ ጃርት፣ ጦጣ፣ ጅብ በአካባቢው ከሚገኙ ዋና ዋና የዱር እንስሳት ትቂቶች ናቸው። ጉሬዛና ዝንጀሮ በቀላሉ ለማየት የሚያስችል አመች ቦታ ነው። በተጨማሪም ዊሊኔክድ ስቶርክ፣ ሃዳድ አይቢሰ፣ ዳክየ፣ ቲክቢልድ ራቨን የመሳሰሉ አእዋፍት በብዛት የሚታዩበት ቦታ ነው (ዝርዝሩን በአባሪ 9.2 ላይ ይመልከቱ)።

3.4. የዳንጉላ ዋሻዎች፣



ምስል 1. በአዊ ብሄረሰብ አስተዳደር ዞን ውስጥ የሚገኙ ዋና ዋና የመስህብ ሃብቶች የሚገኙበትን አካባቢ የሚሳይ ካርታ

የዳንጉላ ዋሻዎች በአንክሻ ጓጉሳ ወረዳ ደንና አችኮሽታ ቀበሌ ውስጥ ከከሳ ግምጃቤት መንገድ 5 ኪሜ ርቀት ላይ 50 ሜትር ገባ ብሎ በ10^{0}52'11" ሰሜን ላቲቲዩድና በ36^{0}56'03" ምስራቅ ሎንግቲውድ ከባህር ወለል በላይ 2441 ሜትር ከፍታ ላይ ይገኛሉ። አራቱም ዋሻዎች በ300 ሜትር ርቀት ያህል በመሬት ውስጥ ለውስጥ የተገናኙ ናቸው። በአካቢቢው ሰዎች ዋሻዎቹ "ደን ዙሪያ ጊዮርጊስ ዋሻ" በሚል ይታወቃሉ። የዋሻዎቹ አካባቢ በአብዛኛው በሰው ሰራሽ ደን የተያዘ ቢሆንም የሐበሻ ግራር፣ የፈረንጅ ግራር፣ ብሳና፣ ፈረንጅ ዕድ፣ ውልክፋ፣ ኮማ፣ በደኑ ውስጥ ከሚገኙ ዕፅዋት መካከል ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ከዚህ ሌላ በዋሻው ውስጥ በኢትዮጵያ እና ኤርትራ ብቻ የሚገኘው ዋትልድ አይቢስ (ባለ እንጥልጥል *ጋጋኖ*) በብዛት የሚታይ ሲሆን የማደሪያና መራቢያ ቦታው እንደሆነ በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል። በተጨማሪም በአካባቢው አንገተ ነጭ እርግብ እና ራሰ ነጭ ጨጭ የሚገኙ ሲሆን ከአጥቢዎች መካከል ሽኮኮ ይገኛል (ዝርዝሩን በአባሪ 9.2 እና 9.3 ላይ ይመልከቱ)።

3.5. የደንደር ፏፏቴ፣ የጋርቾ ፏፏቴ እና የቻግኒ ከተማ አካባቢ፣

እነዚህ ፏፏቴዎች በቻግኒ ከተማ አስተዳደር ውስጥ ይገኛሉ። የዶንደር ፏፏቴ በለወንስ ደገራና በቻግኒ ከተማ 01 ቀበሌ መካከል ልዩ ስሙ መጠለያ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በዶንዶር ወንዝ ከ30-35 ሜትር በሚደርስ ገድል ላይ የሚገኝ ሲሆን የጋርቾ ፏፏቴ ደግሞ በብዝራካኒ ቀበሌ በቻግኒ ድባጤ መንገድ 4.5 ኪሜ ርቀት 900 ሜትር ገባ ብሎ በዱራ ወንዝ ላይ ከ30-40 ሜትር በሚሆን ቁልቁለት ላይ ይገኛል። የዶንደር ፏፏቴ በ10^{0}36'31" ሰሜን ላቲቲዩድና በ36^{0}31'02" ምስራቅ ሎንግቲውድ ከባህር ወለል በላይ 1619 ሜትር ከፍታ ላይ የሚገኝ ሲሆን የጋርቾ ፏፏቴ ደግሞ 10^{0}58'25" ሰሜን ላቲቲዩድና በ36^{0}28'30" ምስራቅ ሎንግቲውድ ከባህር ወለል በላይ 1581 ሜትር ከፍታ ላይ ይገኛል። በእነዚህ አካባቢዎች ከሚታዩ ዕፅዋት መካከል ግራር፣ ሰሳ፣ ዋንዛ፣ ሾላ፣ ችብሃ፣ ዋርካ፣ ብሳና፣ እሸ፣ የቆላ ዋንዛ፣ ዛና፣ ዶቅማ፣ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ከዚህ ሌላ ከአጥቢዎች መካከል ከርከሮ፣ የዱር አሳማ፣ ተራ ዝንጀሮ፣ ጦጣ፣ ተራ ቀበሮ፣ ሚዳቋ፣ ጉሬዛ ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ከአእዋፋት መካከል ርኩም፣ ክሮኖውድ ክሬን፣ ዊሊኔክድ ስቶርክ፣ ጆቢራ፣ *ጋጋኖ*፣ ሄሮን በመስክ ወቅት ከታዩት ውስጥ ትቂቶች ናቸው (ዝርዝሩን በአባሪ 9 ላይ ይመልከቱ)።

3.6. የጓንጓ ኢላላ ጥብቅ የመንግስት ደን፡

ይህ ጥብቅ የመንግስት ደን በቋሚና ጊዚዊ የደን ዘበኞች የሚጠበቅ በጓንጓ ወረዳ ውስጥ 10^{0}52'06" ሰሜን ላቲቲዩድና በ36^{0}35'38" ምስራቅ ሎንግቲውድ ከባህር ወለል በላይ ከ1760 እስከ 2300 ሜትር ከፍታ ላይ የሚገኝ ደን ነው። ከዚህ በፊት ደኑ ወደ 32 ሺህ ሄ/ር የሚገመት ስፍት የነበረው ሲሆን በአሁኑ ስዓት ግን በሰው ሰራሽ ችግሮች በሚደርስበት ጫና ምክንያት በእጅጉ ተመናምኖና ተቆራርጦ ይገኛል። ቦታው በአብዛኛው በተፈጥሮ በቀል ዕፅዋትን የያዘና High Tropical Rainforest ስርዓተ ምህዳርን የሚወክል በክልሉ ምናልባትም ብቸኛ ቅሪት ደን እንደሆነ ይታመናል። ይህ በመሆኑም በሀገራችን ከሚገኙት 58 ትኩረት ከተሰጣቸው (Priority forest area) የመንግስት ደኖች አንዱ ነው።

በደኑ ውስጥ ከሚገኙ ዕፅዋት መካከልም ሰሳ፣ ጥቁር እንጨት፣ ዶንግ፣ ዋንዛ፣ ብሳና፣ ገተም፣ ብርብራ፣ ቆባ፣ ግራር ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ሰሳ ከሁለም የላቀ ድርሻ አለው። በተጨማሪም ድኩላ፣ ነብር፣ ሚዳቋ፣ ጉሬዛ፣ አነር፣ ተራ ዝንጀሮ፣ ጦጣ፣ ጅብ፣ የዱር ዓሳማ፣ ቀበሮ በደኑ ውስጥ ከሚገኙ የዱር እንስሳት መካከል ትቂቶቹ ናቸው። ከዚህ ሌላ ቆቅ፣ ዝግራ፣ ጆቢራ፣ ጭልፊት፣

ዊሊኬክድ ስቶርክ፣ ክሮኖውድ ክሬን፣ የመሳሰሉ አእዋፍት ይገኙበታል (ዝርዝሩን በአባሪ 9 ላይ ይመልከቱ)፡፡

3.7. ትስኪ ፏፏቴ

ይህ ፏፏቴ በዳንግላ ወረዳ አለፋ ካቻ ቀበሌ ከጓንጓ ወረዳ ድንበር አካባቢ በ11^{0}06’52” ሰሜን ላቲቲዩድና በ36^{0}35’53” ምስራቅ ሎንግቲውድ ከባህር ወለል በላይ ከ1788 ሜትር ከፍታ ላይ ይገኛል፡፡ ፏፏቴው በአዊሲና ግዛኒ በተባሉ ወንዞች አማካኝነት የተፈጠረ ነው፡፡ በእዚህ አካባቢ ከሚታዩ ዕፅዋት መካከል ግራር፣ ሰሳ፣ ዋንዛ፣ ሾላ፣ ችብሃ፣ ዋርካ፣ ብሳና፣ እሸ፣ የቆላ ዋንዛ፣ ዛና፣ ዶቅማ፣ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ከዚህ ሌላ ከአጥቢዎች መካከል ከርከሮ፣ ነብር፣ የዱር አሳማ፣ ተራ ዝንጆሮ፣ ጦጣ፣ ተራ ቀበሮ፣ ሚዳቋ፣ ጉሬዛ ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ከአእዋፋት መካከል ስፐር ዊነግድ ጉዝ፣ ክሮኖውድ ክሬን፣ ዊሊኬክድ ስቶርክ፣ ጆቢራ፣ ጋጋኖ፣ ሄሮን በመስክ ወቅት ከታዩት ውስጥ ትቂቶች ናቸው (ዝርዝሩን በአባሪ 9 ላይ ይመልከቱ)፡፡

4. በጥናቱ ጥቅም ላይ የዋሉ ስልቶችና ቁሳቁሶች

4.1. በጥናቱ ጥቅም ላይ የዋሉት ስልቶች

- ከመምሪው ባለሙያዎች ጋር በመሆን ወደ ቱሪዝም ገበያ እንዲገቡ የታሰቡ የመስህብ ቦታዎችን መለየትና ቅድመ ዝግጅት ማድረግ፣
- ከቢሮውና ከመምሪያው ባለሙያዎች ጋር በመሆን ወደ ተመረጡ ቦታዎች በመሄድ በተመረጡት በዶንዶር፣ ጋርቾ፣ ትስኪ እና ፋንግ ፋፋቴዎች፣ በዘንገናና በጥርባ ሃይቆች፣ በወርኪና ዱቲ እርጥብ አዘል መሬቶች የብዝሃ ህይወት ጥናት ማካሄድና መረጃ የማሰባሰብ ስራ መስራት (የመስክ ምልከታ)፣
- በመስክ ሊለዩ የሚችሉትን የዕፅዋት፣ የአእዋፍና የሌሎች እንስሳት አይነት መለየትና ለመለየት አስችጋሪ የሆኑትን ናሙናቸውን መሰብሰብ፣
- የሚታዩ ችግሮችን መለየትና የመፍትሄ ሃሣቦችን ከሚመለከታችው አካላት ጋር በመመካከር የመፍትሄ ሃሣቦችንም ማሰባሰብ፣

4.2. በጥናቱ ጥቅም ላይ የዋሉ ቁሳቁሶች

- የዕፅዋትና እንስሳት መለያ መመሪያ መጽሐፍት፣
- የመስክ መነጽር ባይናኩላር፣
- የፎቶ ዲጅታል ካሜራ፣
- የመገኛ ቦታ መለያ GPS፣

5. በመስክ የተከናወኑ ተግባራት

- ከመምሪያው ባለሙያዎች ጋር በመሆን ስለመስህብ ቦታዎች ሁለተኛ ደረጃ መረጃዎች ተሰብስበዋል፣

- በመስክ ምልከታ የመስህቦቹ ተፈጥሯዊ ገጽታና መገለጫዎቻችው ተመዝግበዋል፣
- በመስህብ ቦታዎች አካባቢ የሚታዩ እፅዋት፣ አእዋፋትና ሉሎች እንስሳት ተመዝግበዋል፣ ፎቶግራፋቸውም ተወስዷል፣
- ለመለየት አስቸጋሪ የሆኑትን ናሙናና ፎቶ በማንሣት ወደ ቢሮ በማምጣት ከሌሎች ዋቢ መጽሐፍት እና ከኢንተርኔት መረጃዎችን በማገናዘብ ተለይተዋል፣
- የመስክ ስራው እንደተጠናቀቀ በመስህቦቹ አያያዝና ችግሮች ዙሪያ ከሚመለከታችው አካላት ጋር ምክክር ተደርጓል (ግብረ መልስ)፣
- በቢሮው ዝርዝር የጥናት ውጤትና ሪፖርት ተዘጋጅቷል፣

6. ከጥናቱ የተገኙ ውጤቶች

በዘንገና ሐይቅና አካባቢው ወደ 49 ዕፅዋት የተመዘገቡ ሲሆን የአማርኛ፣ አገወኛና ሳይንሳዊ መጠሪያቸው በጥንቃቄ እንዲለዩ ተደርጓል (ዝርዝሩን በአባሪ 9 ላይ ይመልከቱ)። የዘንገና ሐይቅና አካባቢውን ጨምሮ በመስክ በተንቀሳቀስንባቸው ሁሉም የመስህብ ሃብቶች ወቅቱ አእዋፍት ለማየት አመች ባለመሆኑ የሚፈለገውን ያህል የአእዋፍት ቁጥር ማየትና መለየት አልተቻለም። ይሁን እንጅ በኮሶበር ከተማ ኮሶበር ሚካኤል ቤተ ክርስትያን፣ በወርኪ እና ዱቲ ዊትላንድስ አካባቢ ከፍተኛ መጠን ያላቸው 30 የአእዋፍት ዝርያዎች ተለይተዋል። ከእነዚህ ውስጥ የጋጋኖ፣ ስቶርክ፣ ኢግሬት፣ ዳክዬ፣ ጆቢራ ዝርያዎች ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ናቸው። እነዚህን የአእዋፍት ዝርያዎች ማየት ለሚፈልጉ ጎብኝዎችም ሆነ ተመራማሪዎች ምቹ ቦታ እንደሆነ ማረጋገጥ ተችሏል። በተጨማሪም ጉሬዛና ሽኮኮ በሐይቁ አካባቢ የተመለከትን ሲሆን በጎብኝዎችም በቀላሉ ሊታዩ የሚችሉ ከአጥቢ እንስሳት መካከል ዋናዎቹ እንደሆኑ ማረጋገጥ ተችሏል።

በፋንግ ፏፏቴ በተመሳሳይ ሁኔታ 51 ዓይነት ዕፅዋት በአማርኛ፣ አገወኛና ሳይንሳዊ መጠሪያቸው የተለዩና የተመዘገቡ ሲሆን 9 የአእዋፍት ዝርያዎች፣ ጉሬዛና ጦጣ ተለይተዋል። በተለይም ከአእዋፍት መካከል ባለ እንጥልጥል ጋጋኖ፣ አንገተ ነጭ እርግብ እና ራሰ ጥቁር ጨጭ እንደልብ የሚታዩ ዝርያዎች ናቸው።

በጥርባ ሐይቅና አካባቢው 56 ዓይነት የዕፅዋት ዝራያዎች የተለዩ ሲሆን የዕፅዋት ሽፋኑ ከጓንጓ ኢላላ ቀጥሎ በዚህ የመስክ ምልከታ ከታዩ የመስህብ ሃብቶች ጋር ሲነፃፀር የተሻለ እንደሆነ ማረጋገጥ ተችሏል። በዚህ አካባቢ ከፍተኛ መጠን ባይኖረውም በመጥፋት ለይ ያለው የዝግባ ዕፅዋት ይገኛል። ከዚህ ሌላ 18 የአእዋፍት ዝርያዎች ተለይተዋል። ተራ ዝንጀሮና ጉሬዛ በአካባቢው እንደልብ የሚታዩ አጥቢ የዱር እንስሳት ናቸው።

በዳንጉላ ዋሻ 25 የዕፅዋት ዝርዎች የተለዩ ሲሆን አባዛኛው ቦታ በሰው ሰራሽ ደን የተሸፈነ እንደሆነ መመልከት ችለናል። በዋሻዎቹና በግምጃ ቤት ከተማ አካባቢ 15 ዓይነት የአእዋፍት ዝርያዎች የለየን ሲሆን በተለይም በዋሻዎቹ ውስጥ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ባለ እንጥልጥል ጋጋኖ መመልከት ችለናል። የመኖሪያና መራቢያ ቦታው እንደሆነም ማረጋገጥ ተችሏል።

ጋርቾ ፏፏቴ አካባቢ 38 ዓይነት ዕፅዋት የተመለከትን ሲሆን የዕፅዋት ሽፋኑም ጥሩ እንደሆነ አረጋግጠናል። በዶንደር ፏፏቴ አካባቢ ደግሞ 37 ዓይነት ዕፅዋት ተለይተዋል። በቻግኒ ከተማና በአካባቢው 14 ያህል የአእዋፍት ዝርዎች ተለይተዋል። በተጨማሪም በጓንጓ ኢላላ አካባቢ 44 ዓይነት ዕፅዋት የተለዩ እና በዕፅዋት ሽፋኑ ከሁሉም የመስህብ ሃብቶች የተሻለ ቢሆንም ቀደም ሲል ከነበረው ይዘት በጣም እየተራቆተ እንደሆነ ማረጋገጥ ተችሏል።

በትስኪ ፏፏቴ አካባቢ 45 ዓይነት ዕፅዋት የተለዩ ሲሆን 18 ያህል የአእዋፍት ዝርያዎች፣ ጉሬዛና ዝንጆሮን ጨምሮ ሌሎች የዱር እንስሳት እንደሚገኙ አረጋግጠናል።

በአጠቃላይ በዚህ ጥናት ከ100 በላይ ዕፅዋት፣ 39 ያህል አእዋፋት እና 13 ያህል አጥቢ እንስሳት የተለዩ ሲሆን የአማርኛ፣ አገወኛና ሳይንሳዊ መጠሪያቸው ጥቅም ላይ ሊውል በሚችልበት መንገድ ተዘጋጅቷል (ዝርዝሩን በአባሪ 9 ውስጥ ይመልከቱ)።

7. በመምሪያው ወደ ፊት መከናወን ያለባቸው ተግባራት

- በአሁኑ ወቅት በዘንገና ሐይቅ አካባቢ የተደራጁ አስጎብኝ ወጣቶች ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ ሀገር ከመጡ ቱሪስቶች ከመግቢያ ዋጋ ብቻ ከሚቀበሉት ገቢ የሚያገኙ ቢሆንም ከዘርፉ የሚያገኙትን ጥቅም ለማሻሻልና ለማሳደግ ለአስጎበኙበት ተገቢውን ክፍያ የሚጠይቁበትና ገቢያቸውን የበለጠ የሚሳድጉበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
- የጋርቾ ፏፏቴ የጎብኝዎችን ቀልብ ሊስብ የሚያስችል ገፅታ ባለቤት ቢሆንም ቦታው ድረስ ገብቶ ጉብኝትም ሆነ ጥናት ለማካሄድ አስቸጋሪ መሆኑ ለጉብኝት ምቹ ማድረግ ያስፈልጋል፣
- የጓንጓ ኢላላ የመንግስት ደን ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰበት ስለሆነ ከሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤትና የአካባቢው ህብረተሰብ ጋር በመተባበር የጥበቃና ልማት ስራ ማካሄድ፣
- የብሄረሰብ ዞኑ እምቅ የቱሪስት መዳረሻ ያለው ቢሆንም በሚፈለገው መጠንና የአካባቢው ህብረተሰብ ከዘርፉ ጥቅም ሊያገኝ በሚያስችለው ሁኔታ የተደራጀ ባለመሆኑ ከመቂትና ከሌሎች አቻ አካባቢዎች ስለ ኢኮ-ቱሪዝም ማህበራት አደረጃጀት፣ አሰራርና ስለ ቱሪስት መዳረሻዎች ልማትና አጠቃቀም ተሞክሮ መውሰድ፣

8. ያጋጠሙ ችግሮች

- መስክ የወጣንበት ወቅት አእዋፍትን ለማግኘትና ለመለየት ያላስቻለን መሆኑ፣
- የጋርቾ፣ ጓንጓ ኢላላ እና ትስኪ ፏፏቴዎች አካባቢ ሁሉም ቦታዎች በጥናቱ ያልተዳሰሱ መሆኑ እና ተጨምሪ ጥናት የሚጠይቁ መሆኑ፣
- አልፎ አልፎ ያሉ መንገዶች ለተሽከርካሪ አስቸጋሪ የነበሩ መሆኑ፣

9. አባሪ

9.1. List of Plants Registered in and around Tourist attraction sites in Awi Zone

No.	Scientific Name	Vernacular name		Tourist attraction sites								Remark
		Amharic Name	Awigna	1	2	3	4	5	6	7	8	
1.	*Acacia abyssinica*	Girar	Tsatsi	√	√	√	√	x	x	√	x	
2.	*Acacia decurrens*	Yeferenji grar	Ferenji Tsatsi	√	x	√	√	x	x	x	x	
3.	*Acacia lahai*	Cheba	Tsivi	√	√	√	x	x	x	x	x	
4.	*Acacia seyal*	Girar	Sasi	x	x	x	x	√	x	x	x	
5.	*Acanthus eminens*	Kosheshilla	Danduri	x	x	√	x	√	√	√	√	
6.	*Acanthus sennii*	Kosheshilla	Danduri	√	√	√	x	x	x	x	x	
7.	*Albiza malacophylla*	Sendel	-	x	x	x	x	√	√	x	x	
8.	*Albizia gummifera*	Sesa	Kansini	x	√	√	x	√	√	√	√	
9.	*Apodytes dimidiate*	Dong	Zindi	√	√	√	x	x	x	x	x	
10.	*Argyrolobium schimperianum*	Amedmado	Amedmadi	√	√	x	x	x	x	x	x	
11.	*Arundinaria alpine*	Kerkeha	Anini	√	√	x	x	x	x	x	x	
12.	*Asparagus africanus*	Yeset kest	-	x	√	x	x	x	x	x	x	
13.	*Bersama abyssinica*	Azamira	Dinkifi	√	√	√	x	√	√	√	√	
14.	*Bidens spp*	Aday abeba	-	x	x	√	x	√	√	√	√	
15.	*Bridelia micrantha*	Yeneber Tifer	-	x	x	x	x	x	√	x	x	
16.	*Brucea antidysenterica*	Yedega Avalo	Avali	√	√	√	√	√	√	√	√	
17.	*Buddleja polystachya*	Anfar/Ashiquar	Ashiquari	√	√	√	√	x	√	√	√	
18.	*Calpurnia aurea*	Ligta	Zimaki	√	√	√	x	x	x	√	x	
19.	*Capparis tomentosa*	Gumero	Weri/ Hanguri	x	x	x	x	√	√	√	√	
20.	*Carissa edulis*	Agam/Gumero	Qawa/Atry	x	x	√	x	x	√	√	√	
21.	*Celtis Africana*	Sarengi/Qawet	Sarengi/Equa	x	x	√	x	x	√	x	√	
22.	*Clausena anistata*	Limich	Luntsi	√	√	√	√	x	x	√	√	
23.	*Clematis simensis*	Azo Hareg	Azu Ahiera	√	√	√	x	√	√	√	√	
24.	*Clutia abyssinica*	Fiyelefegi	Chenfoch	√	√	√	√	x	x	√	√	
25.	*Combretum collinum*	Abalo	-	x	x	x	x	√	x	x	x	

No.	Scientific Name	Vernacular name		Tourist attraction sites								Remark
		Amharic Name	Awigna	1	2	3	4	5	6	7	8	
26.	*Combretum molle*	Abalo	Abalo	x	x	x	x	√	x	x	x	
27.	*Cordia Africana*	Wanza	*Bugtsi*	x	x	√	x	√	√	x	√	
28.	*Croton macrostachyus*	Bisana	Asisi	√	√	√	√	√	√	√	√	
29.	*Cupressus lusitanica*	Yeferenji tsid	Yeferenji Tsidi	√	x	√	√	x	x	x	x	
30.	*Cynodon dactylon*	Serdo	Sierdu	√	√	√	√	x	x	√	x	
31.	*Cyperus spp*	Gramita	Gramiti	√	√	√	√	x	√	√	x	
32.	*Discopodium penninervum*	Alumma/Ameraro	Alumi	√	√	√	x	x	x	√	x	
33.	*Dombeya torrid*	Wulkifa	Tsari	√	√	√	√	x	√	√	√	
34.	*Dovyalis abyssinica*	Koshim/Aguam	Aguami	√	√	√	x	x	x	x	√	
35.	*Dracaena steudneri*	Tsepatos	Emdarch/Debekeded	x	x	√	x	x	x	√	x	
36.	*Echinops giaganteus*	Dindro	-	x	x	x	x	√	x	√	x	
37.	*Ekebergia capensis*	Entatay	Churi	√	√	x	x	x	x	x	x	
38.	*Embelia schimperi*	Enkoko	Enqoku/enqoki	√	√	√	√	x	x	√	x	
39.	*Enset Ventricosum*	Enset	Gangi	√	x	√	x	x	x	√	x	
40.	*Entada abyssinica*	Ambelta	-	x	x	x	x	x	√	x	x	
41.	*Ephorbia abyssinica.*	Qulqual	Kulkuli	√	√	√	x	x	x	√	x	
42.	*Erythrina brucei*	Korch	Buri	√	√	x	x	x	x	x	x	
43.	*Eucalyptus camaldulensis*	Key bahir zaf	Bar zaff	x	x	√	x	x	x	x	x	
44.	*Eucalyptus globules*	Nech Bahir Zaf	Bar zaff	√	√	√	x	x	x	x	x	
45.	*Ficus carica*	-	Enqui	x	x	√	x	x	x	x	√	
46.	*Ficus sur (F. capensis)*	Shola	Emuwi	√	√	√	x	√	√	x	√	
47.	*Ficus sycomorus*	Shola	Emuwi	x	x	x	x	√	x	x	x	
48.	*Ficus thonningii*	Chibha	Siwawi	x	x	x	x	√	x	√		
49.	*Ficus vasta*	Warka	Bukti	x	x	√	x	√	√	√	√	
50.	*Galiniera saxifrage*	Yetota Kula	-	x	√	x	x	x	x	x	x	
51.	*Gardenia volkensii*	Gambilo	Durkai	x	x	x	x	√	√	x	√	
52.	*Grewia ferruginea*	Lenkoata	Sankui	x	x	x	x	√	√	√	√	
53.	*Grewia villosa*	Lenkoata(Yeshinasha)	Tsanquai	x	x	x	x	x	√	√	x	
54.	*Hagenia abyssinica*	Kosso	Shinchi	√	√	x	x	x	x	x	x	

No.	Scientific Name	Vernacular name		Tourist attraction sites								Remark
		Amharic Name	Awigna	1	2	3	4	5	6	7	8	
55.	*Hibiscus micranthus*	Nacha	Nacha	x	√	√	x	x	x	√	√	
56.	*Impatiens sp*	Gurshit	Ensosili	x	√	√	√	√	√	√	√	
57.	*Jasminum abyssinicum*	Abit areg	-	x	√	x	x	x	x	x	x	
58.	*Juniperus procera*	Yabesha Tsid	Yabesha Tsidi	x	x	√	x	x	x	x	x	
59.	*Justicia schimperiana*	Simiza	Lili	√	√	√	√	x	x	√	x	
60.	*Kalanchoe petitiana*	Andahula	Anduqi	√	√	√	√	x	x	√	√	
61.	*Leonotis sp.*	Yeferse zeng	-	√	x	x	x	x	x	x	x	
62.	*Lippia sp*	Kesign	-	x	√	x	x	x	x	x	x	
63.	*Maesa lanceolata*	Qilabo	Kimbi	√	√	√	√	√	√	√	√	
64.	*Maytenus arbutifolia*	Atat	Koki	x	x	x	x	√	√	x	x	
65.	*Milletia ferruginea*	Birbra	Chibign	x	x	x	x	x	x	√	√	
66.	*Mimusops kummel*	Eshe	Enkui	x	x	x	x	√	x	x	√	
67.	*Mytenus senegalensis*	Qoba	Koki	√	√	√	√	x	x	√	x	
68.	*Olea sp.*	Weira	Wiri	√	x	x	x	x	x	x	√	
69.	*Phoenix reclinata*	Selen	-	x	x	x	x	x	√	x	√	
70.	*Phytolacca dodecandra*	Indod	Sebeti	x	x	x	√	x	x	x	x	
71.	*Pilostigma thonningii*	Yekolla wanza	Dabdi	x	x	x	x	√	x	x	x	
72.	*Pinus patula*	Pinus	Patulla	√	x	x	x	x	x	x	x	
73.	*Pittsporium viridiflorum*	Dingay seber	Ashangibi/Galmaksi	√	√	√	x	√	√	√	√	
74.	*Podocarpus falcatus*	Zigba	Eji	x	x	√	x	x	x	x	√	
75.	*Premnatoma laxiflora*	Shesheki/ wenbella	Baguri/ Wenbelli	x	x	x	x	√	x	x	√	
76.	*Protea gaguedi*	Awura	Kisingi	x	x	x	x	x	x	√	x	
77.	*Prunus africanus*	Koma/ Tikur enchet	Damtsi	√	√	√	√	√	√	x	√	
78.	*Pterolobium stelluatum*	Agemetry/ Kentefa	Entivi	x	x	√	x	√	√	√	√	
79.	*Rhoicissus tridentata*	Yewef abeba	Deichiha kampa	x	x	x	x	x	x	x	√	
80.	*Rhus glutinous*	Embus kamo	Kumini	x	x	x	x	√	√	x	√	
81.	*Rhus vulgaris*	Ashikamo	Ashikuri/Kumani	x	√	√	x	√	√	√	√	
82.	*Rosa abyssinica*	Kega	Gimsi/Gimtsi	√	x	x	x	x	x	x	x	
83.	*Rubus apetalus*	Enjori	Enjorie	√	√	√	x	x	x	x	x	

No.	Scientific Name	Vernacular name		Tourist attraction sites								Remark
		Amharic Name	Awigna	1	2	3	4	5	6	7	8	
84.	*Rumex nervosus*	Embacho	Ambuach	x	√	√	√	x	x	x	x	
85.	*Salix subserrata*	Kaya/ Shinshina	Tsutsuwi	x	√	x	x	√	x	x	x	
86.	*Schefflera abyssinica*	Getum	Pimpini	√	√	√	x	x	x	√	√	
87.	*Sida ovata*	Chifrig	Kinchuti	x	x	x	x	x	x	√	x	
88.	*Solanecio gigas*	Bozz	Bozz	√	√	√	√	x	x	x	x	
89.	*Solanum marginatum*	Yegeber Embuway	Empapi	x	x	x	x	x	√	x	x	
90.	*Solanum sp.*	Embuwoy	Embuwoy/ Empapi	x	x	√	x	x	x	√	√	
91.	*Stephania abyssinica*	Yeayit hareg	Yintsi ahiera	√	√	X	√	x	x	x	x	
92.	*Stereospermum kunthianum*	Zana	Zani	x	x	X	x	√	√	x	√	
93.	*Syzygium guineense*	Dokima	Bagusti	x	x	X	x	√	√	x	√	
94.	*Teclea nobilis*	Sini	Sila	√	√	√	x	x	x	x	√	
95.	*Tragia pungens*	Kusha	Avaviri	√	√	√	√	x	x	√	√	
96.	*Urera hypselodendron*	Lankusho/Lankuso	Lanqshi	√	√	√	√	√	√	√	√	
97.	*Urtica simensis*	Sama	Siri	√	X	x	x		x	x	x	
98.	*Vernonia amygdalina*	Grawa	Koqitsi	√	√	√	√	√	√	√	√	
99.	*Ximenia Americana*	Enkoy	Enkuli	x	X	x	x	√	x	x	x	
100.	*Zehneria scabra*	Areg resa	Eha-ahiera	√	√	√	x	x	x	x	x	
101.	*Ziziphus mucronata*	Foch	Fochi	x	X	x	x	√	√	x	x	
	Total			49	51	56	25	38	37	44	45	

Note: 1. Lake Zengena, 2. Fang Waterfall, 3. Lake Tirba, 4. Dangula Natural Cave, 5. Garcho waterfall, 6. Dondor waterfall, 7. Guangua Ellala priority forest area, 8. Tiski Waterfall

√= Seen, X= Not Seen

9.2. List of Birds Registered in and around Tourist attraction sites in Awi Zone

No.	Common Name	Scientific Name	T/attraction sites						Remark
			1	2	3	4	5	6	
1	Egyptian goose	*Alopochen aegyptiaca*	√	x	√	x	x	√	ዳክዬ
2	Tawny eagle	*Aquila rapax*	√	x	√	√	x	x	ጭልፊት
3	Grey heron	*Ardea cinerea*	√	x	x	x	√	x	
4	Blak headed heron	*Ardea melanocephala*	x	x	x	x	√	√	
5	Crowned crane	*Balearica regulorum*	x	x	x	x	√	√	
6	Wattled ibis	*Bostrychia carunculata*	√	√	√	√	x	x	ባለ እንጥልጥል ጋጋኖ
7	Cattle egret	*Bubulcus ibis*	√	√	x	x	√	√	
8	Abyssinian ground hornbill	*Bucorvus abyssinicus*	x	x	x	x	√	x	ርኩም
9	Silvery-cheeked Hornbill	*Ceratogymna brevis*	√	x	√	x	√	x	
10	Pied king fisher	*Ceryle rudis*	√	x	x	x	x	x	
11	Woolly necked stork	*Ciconia episcopus*	√	x	√	√	√	√	
12	White collard pigeon	*Columba albitorques*	x	√	x	√	x	x	አንገተ ነጭ ርግብ
13	Speckled pigeon	*Columba guinea*	√	√	x	√	√	√	ርግብ
14	Pied crow	*Corvus albus*	√	x	x	√	x	x	ቁራ
15	Cape rock	*Corvus capensis*	√	√	√	x	x	√	ቂራ
16	Thick billed raven	*Corvus crassirostris*	√	x	√	√	x	x	ቁራ
17	Little egret	*Egretta garzetta*	√	x	x	x	x	x	
18	White backed vulture	*Gyps bengalensis*	√	x	√	√	√	√	ጆቢራ
19	Hadad ibis	*Hagedashia hagedash*	√	x	√	√	x	√	ጋጋኖ
20	Black winged stilt	*Himantopus himantopus*	√	x	x	x	x	x	
21	Yellow billed stork	*Ibis ibis*	√	x	x	x	x	x	
22	Blue eared glossy starling	*Lamprotornis chalybaeus*	√	√	√	√	√	√	
23	Blue-breasted bee eater	*Merops variegatus*	x	x	x	x	x	√	
24	Black kite	*Milvus migrans*	√	x	√	√	x	x	
25	Hooded vulture	*Necrsyrtes monachus*	√	x	√	√	√	√	ጆቢራ
26	Tacazze sunbird	*Nectarinia tacazze*	x	x	√	x	x	x	
27	Dark-headed oriole	*Oriolus monacha*	√	√	√	√	x	√	አንገተ ጥቁር ጨጭ
28	Swainson's sparrow	*Passer swainsonii*	√	√	√	√	√	√	
29	White pelican	*Pelecans onocratalus*	√	x	x	x	x	x	
30	Cormorant	*Phalacrocorax sp.*	√	x	x	x	x	x	አሳ ወጊ
31	African Spoon bill	*Platalea alba*	√	x	x	x	x	x	
32	Spur winged goose	*Plectopterus gambensis*	x	x	x	x	x	√	
33	Secretary bird	*Sagittarius serpentarius*	x	x	x	x	x	√	
34	Hamerkop	*Scopus umbretta*	√	x	√	x	x	x	
35	Ring-necked dove	*Streptopelia capicola*	√	√	√	√	√	√	
36	White-cheeked Turaco	*Tauraco leucotis*	√	x	x	x	x	x	
37	Sacred ibis	*Threskiornis aethiopicus*	√	x	x	x	√	√	ጋጋኖ
38	Hemprich's Horn bill	*Tockus hemprichii*	x	x	√	x	x	x	
39	Spur winged plover	*Vanellus spinosus*	√	x	x	x	x	x	
	Total		30	9	18	15	14	18	

Note: 1. Lake Zengena, 2. Fang Waterfall, 3. Lake Tirba, 4. Dangula Natural Cave and Gimjabet town, 5. Garcho and Dondor waterfalls and Chagni town, 6. Tiski Waterfall

√= Seen, X= Not Seen

9.3. List of Mammals Observed by Locals and study team

No	Common Name	Scientific Name	1	2	3	4	5	6	7	Remark
1.	Common/Golden	*Canis aureus*	x	x	√	x	√	√	√	ቀበሮ
2.	Vervet monkey	*Cercopithecus aethiops*	x	√	√	x	√	√	√	ጦጣ
3.	Abyssinian colobus	Colobus guereza	√	√	√	x	√	√	√	ጉሬዛ
4.	Spotted Hyena	*Crocuta crocuta*	√	x	√	x	√	√	√	ጅብ
5.	Stripped hyena	Hyaena hyaena	√	x	√	x	√	√	√	ጅብ
6.	Porcupine	*Hystrix cristata*	x	x	√	x	√	√	√	ጃርት
7.	Leopard	*Panthera pardus*	x	x	x	x	x	√	√	ነብር
8.	Anubis baboon	*Papio anubis*	x	x	√	x	√	√	√	ዝንጀሮ
9.	Common warthog	*Phacochoerus aethiopicus*	√	x	√	x	√	√	√	ከርከሮ
10.	Rock Hyrax	*Procavia capensis*	√	x	√	√	√	√	√	ሽኮኮ
11.	Wild pig	*Sus scrofa*	x	x	√	x	√	√	√	የዱር ዓሳማ
12.	Common duiker	*Sylvicapra grimmia*	x	x	√	x	√	√	√	ሚዳቋ
13.	Common bushbuck	*Tragelaphus scriptus*	x	x	√	x	√	√	√	ድኩላ
		Total	5	2	12	1	12	13	13	

Note: 1. Lake Zengena, 2. Fang Waterfall, 3. Lake Tirba, 4. Dangula Cave,
5. Garcho and Dondor waterfalls, 6. Guangua Elala priority forest area, 7. Tiski Waterfall
√= Seen, X= Not Seen

9.4 Photographi representation of Birds seen in Awi Zone



Egyptian goose



Tawny eagle



Wattled ibis



Grey heron



Cattle egret



Silvery-cheeked Hornbill



Pied king fisher



Speckled pigeon



Pied crow



Thick billed raven



Wooly necked stork



Little egret



Cape rook



Black winged stilt



White backed vulture



Hadad ibis



Yellow billed stork



Blue eared glossy starling Black kite Hooded vulture



Dark headed oriole Swainson's sparrow White pelicans



African Spoon bill Hamerkop Ring-necked dove



White-cheeked Turaco Sacred ibis Spur winged plover Tacazze sunbird



Hemprich's Horn bill



Black headed heron



Crowned crane



Abyssinian ground hornbill



Spur winged goose